ለእናንተ ያለው የእግዚአብሄር መሰረታዊ የፍቅር እውነት

# እንደምወዳቸው ንገራቸው



JOYCE MEYER

ጆይስ ማየር

የኒው ዮርክ ታይምስ ቁ. 1 ጸሐፊ

# እንደምወዳቸው ንገራቸው

*በጆይስ ማየር*

*የእግዚአብሔርን ስጦታ ይፈልጉ - ገደብ የለሽ ፍቅር!*

General Information
About the Original Book

# TELL THEM I LOVE THEM

RECEIVING A REVELATION OF GOD'S LOVE FOR YOU

BY
JOYCE MEYER

Publisher:
Warner Books Edition
Copy right @ 1995 by Joyce Meyer
Life in the Word, Inc
P.O.Box 655
Fenton, Missoure 63026
USA

Information About The

Amharic Translated Version
Publisher:

**ማውጫ ........................................................ ገጽ**


መግቢያ ........................................................ 1

እግዚአብሔር ይወድሃል........................................ 2

ብቁ ነኝ........................................................ 5

ፍቅር ኅብረት ነው............................................ 11

ፍቅር፣ መታመንና እምነት................................... 15

ከፍርሃት ነጻ መሆን ........................................... 19

ፍቅር ለሌላው ያስባል......................................... 22

የእግዚአብሔር ፍቅር ይለውጥሃል.......................... 27

# መግቢያ

ሰዎች የእግዚአብሔር ፍቅር መገለጥ ከምንም ነገር በላይ እንደሚያስፈልጋቸው አምናለሁ፡፡ ይህም በክርስትና ሕይወት በድል ለመኖር መሠረት  እንደሆነ አምናለሁ፡፡ ስለ እግዚአብሔር ፍቅር የሚያስፈልገን የአእምሮ ዕውቀት አይደለም፤ የሚያስፈልገን መገለጥ ነው፡፡ ይህ የሚሰጠው በመንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው፤ የሚሰጠውም እያንዳንዱ አማኝ የእግዚአብሔርን ፍቅር ሲያሰላስል፣ በራሱ ሕይወት የእግዚአብሔርን ፍቅር ሲመለከትና ይህንንም መገለጥ በእግዚአብሔር ቃልና በጸሎት አማካይነት ሲፈልግ ነው፡፡

ኢየሱስ ለዓለም ሁሉ እንዲሞት እግዚአብሔር የላከው ዓለምን ስለሚወድ መሆኑን ለመረዳት አዳጋች አይደለም፡፡  በዚህ ምድር ላይ የምትኖረው አንተ ብቻህን ቢሆን ኖሮ እግዚአብሔር ስለሚወድህ ለአንተ ብቻ እንዲሞትልህ ኢየሱስን  ልኮታል ብሎ ማሰብ አስቸጋሪ አይሆንም፡፡

ከብዙ ተስፋ የቆረጠ የክርስትና ህይወት ከኖርኩ በኋላ የእግዚአብሔርን ፍቅር መረዳት ቻልኩ፡፡   እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ከጸጋው የተነሣ ፍቅሩን ገለጠልኝ፡፡ ታዲያም ይህ መገለጥ መላውን ሕይወቴንና አረማመዴን ለወጠው፡፡

ይህን መጽሐፍ ስታነቡ ስለ እግዚአብሔር ፍቅር አዲስ ዕይታና መረዳት ታገኛላችሁ ብዬ አምናለሁ፡፡ ያገኛችሁት መረዳትና መገለጥ ስለ እግዚአብሔር ፍቅር የውስጥ ረሀብ ይፈጥርባችኋል ብዬ አምናለሁ፡፡ መጽሐፏን በእርጋታ እንድታነቡ፣ ለጥናት አጋዥ መጽሐፍት አድርጋችሁ እንድትጠቀሙበ የእግዚአብሔርን ቃል እንድታሰላስሉበትና በቀጣይ ገጾች የምታገኟቸውን ትምህርቶች እንድታጤኑ እመክርሃለሁ፡፡

ይህን መጽሐፍ እንድታነቡ ስጋብዝ በታላቅ ትህትና፤ ያለ እርሱ ምንም እንዳልሆንህ በመረዳትና ስለ ቃሉ አንዳች መገለጥ ወይም መረዳት ቢኖረን ከጸጋው የተነሳ መሆኑን በመገንዘብ እንዲሆን ምኞቴ ነው፡፡

# 1.እግዚአብሔር ይወድሃል!

"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው
እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ
ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና"

ዮሐ 3÷16

እግዚአብሔር ቤተሰብ ስለሚፈልግ ልጆቹ እንድንሆን አደረገን፡፡ እግዚአብሔር እንደ ልጆቹ እንጂ ሕፃናት እንድንሆን አይሻም፡፡ ነገር ግን እርሱ እንድንሆን የሚፈልገው እንደ ልጆቹ ነው፡፡ በእርሱ ላይ እንድንደገፍ፣ እንድንመረኮዝና እንድናርፍ ይፈልጋል ደግሞም እንድንወደውና እርሱም እንዲወደን ይፈልጋል አንዳች የሚያስፈልገን ነገር ሲኖር በእርሱ እንድነታመንና ወደ እርሱም እንድንመጣ ይፈልጋል፡፡ እርሱ ከአንተ ጋር ኅብረት ለመመስረት ይፈልጋል፡፡

ብዙዎቻችን ዮሐንስ 3÷16 የምንመለከተው ሰፋ ባለ ትርጉሙ ነው፡፡"እርግጥ ነው ኢየሱስ ለዓለሙ ሁሉ እንደሞተ አውቃለሁ" እንላለን፤ ነገር ግን ኢየሱስ ለመላው ሕዝብ ብቻ አይደለም፤ እርሱ ለእያንዳንዳችን ሞቷል፤ እርሱ ለአንተም ሞቷል!

በዚህ ምድር የምትኖረው አንተ ብቻ ሆነህ ቢሆን ኖሮ፣ ስለ አንተ ብቻ ክርስቶስ ይሞት ነበር፡፡ ለአንተ ብቻ ይህን ሁሉ መከራ ይቀበል ነበር፡፡ እርሱ ለአንተ ሞቷል! እግዚአብሔርም በዘላለማዊ ፍቅሩ እጅግ ይወድሃል፡፡

አንድ ቀን በመኪናዬ እየተጓዝኩ እግዚአብሔር ለልቤ እንዲህ ሲል ተናገረኝ፤ "ጆይስ አንቺ የዐይኔ ብሌን ነሽ"፡፡ ይህ ሐሳብ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዳለ እንኳ አላውቅም ነበር፡፡ ዲያቢሎስ ወደያው አንድ የተለየ ሐሳብ ይዞ መጣ፤ "ይህ ቅልጥጥ ያለ ትዕቢት አይደለም እንዴ? ለመሆኑ አንቺ ማን ነሽ? አለኝ፡፡ከዚያም ወደ ራሴ ተመለስኩኝና "እንደዚህ ማሰብ አይገባኝም ነበር"አልኩ፡፡ራሳችንን የተለዩ ሰዎች፣ ክህሎት የተሰጠንና ልዩ ሰው አድርጎ ማሰብ ከሥጋዊ አስተሳሰባችን ጋር ይቃረንብናል፡፡ እያንዳንዳችን ከሌላው ሰው የተለየ ሰው ተደርገን በአባታችን በእግዚአብሔር ተፈጥረናል፡፡

ይህን ጉዳይ ሳሰላስል ሳለ እግዚአብሔር በአንድ የገበያ አዳራሽ ውስጥ ብርቱካን የምትገዛ ሴት በኅሊናዬ እንዳስብ አደረገኝ፡፡ ሴቲቱ ሁሉንም ከተመለከተች በኋላ ከሁሉም የሚበልጠውን ምርጥ ብርቱካን ወሰደች፡፡ እንግዲህ እግዚአብሔር እየተናገረኝ ያለው ለእርሱ ምርጥ ብርቱካን መሆኔን ነው፡፡ ለእርሱ ልዩ ሰው ነኝ፡፡

ይህ ትክክለኛ አባባል ላይመስል ይችላል:: ነገር ግን እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችን የሚለን ይሄንኑ ነው። እግዚአብሔር እየተናገረ ያለው አንተ ምርጥና ግሩም ሰው እንደሆንህና ሌሎች ሰዎች በሙሉ ምንም እንደማይጠቅሙ አይደለም። እርሱ እየተናገረ ያለው ሁላችንም ልዩ ሰዎች መሆናችንን ነው። ይህ በቃሉ ውስጥ አለ፤ ቃሉም ለሁላችንም ተሰጥቷል። አንተ የእግዚአብሔር ዐይን ብሌን ነህ።

ስለ ራሴ መልካም ነገር ያሰብሁ ስለ መሰለኝና ውስጤም ስለ ወቀሰኝ እግዚአብሔር የተናገረውን ነገር አልተቀበልኩትም። ከሁለት ቀን በኂላ መጽሐፍ ቅዱሴን ስከፍት ዐይኔ መዝሙር 17÷8 ላይ አረፈ ቃሉም ፍጥጥ ብሎ አየኝ፤ "እንደ ዐይን ብሌን ጠብቀኝ፤ በክንፎችህ ጥላ ሰውረኝ"። "እንደምን ያለ አስገራሚ አባባል ነው፤ ይህን እኮ የተናገረው እግዚአብሔር ነው፤ እኔ የእግዚአብሔር የዐይኑ ብሌን ነኝ" አልሁ። ይህን ባሰብሁ ቁጥር ለረጅም ጊዜ የተለየሁ ሰው እንደሆንሁ ይሰማኝ ነበር።

ሰዎች በልባቸው የመወደድ መሻትና ፍላጎት አላቸው። እግዚአብሔር ሲፈጥረን እንዲህ እንድንሆን አልሞ ነው። ብዙ ሰዎች እግዚአብሔር ኢየሱስንም ዓለምንም እንደሚወድ ያምናሉ፤ ሆኖም እነርሱን ግን እንደሚወድ ለመረዳት ይቸገራሉ። ይሁንና ቃሉ የሚያስተምረን እግዚአብሔር ኢየሱስን እንደሚወድ ሁሉንም ይወዳል። እርሱ ኢየሱስን እንደሚወድ አንተንም ይወድሃል። ዩሐንስ 5÷20 እንመልከት

"አብ ወልድን ይወዳልና፤ የሚያደርገውንም ሁሉ ያሳየዋል
እናንተም ትደነቁ ዘንድ ከዚህ የሚበልጥ ሥራ ያሳየዋል"።

እዚህ ላይ እግዚአብሔር እንዲህ በማለት እየተናገረ ነው፤ "እነዚህን ሁሉ ታላላቅ ነገሮች ያደረግሁት በኢየሱስ በኩል ነው፤ ሁላችሁም እንድትደነቁ ከዚህ የሚበልጥ ነገር በእርሱ በኩል አደርጋለሁ" (የደራሲዋ አገላለጽ)። በአንድ የሆነ ነገር መደነቅ፣ እግዚአብሔርም በሚያደርገው ነገር መገረም መልካም እንደሆነ ታውቃለህ?

እነዚህን የመሳሰሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እናነባለን፤ ይሁንና አብዛኛውን ጊዜ እግዚአብሔር ለእኛ ሊያደርግ የሚፈልገውን ነገር አናስተውልም። በኢየሱስ በኩል ያደረጋቸውን ታላላቅ ሥራዎች ተመልክተን እንድንደነቅና "እግዚአብሔር ሆይ በኢየሱስ በኩል ያደረግኸው ነገር ድንቅ ነው" እንድንል ይፈልጋል። ከዚያም ወደ ዮሐንስ 14÷12 ሄደን ኢየሱስ እንዲህ

በማለት የተናገረውን እንድናነብ ይፈልጋል፤ "በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል፤ ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል፤ እኔ ወደ አብ እሄዳለሁና"።

እግዚአብሔር ይህንኑ በአንተም ውስጥ ያደርጋል፤ ደግሞም ኢየሱስ ወደ አባቱ ስለሄደ እርሱ ከሰራውም በላይ በአንተ ውስጥ ያደርጋል።ይህን ታምናለህን? እግዚአብሔር እንደሚወድህና በአንተም በኩል ሊሠራ እንደሚፈልግ በእርግጥ ታምናለህ?

አንድ ቀን መጽሐፍ ቅዱሴን ሳጠና እግዚአብሔር እንዲህ የሚል ነገር አስተማረኝ፤ "ጆይስ ሰዎችን ስለምወድ በየቀኑ ለሰዎች ብዙ ነገር አገርጋለሁ፤ እነርሱ ግን ሊመለከቱ አልቻሉም። ጨርሶም ሊያስተውሉ አልቻሉም። አንድ ምሳ ልስጥሽ። በየቀኑ ፀሐይን "ውጪ" ብዬ ሳዝ፣ ይህን የማደርገው ለጆይስ፣ ለቤቲ፣ ለጄሚ፣ ለ……(የራስህን ስም ሙላ) ብዬ ነው" አለኝ።

እስቲ ቆም ብለህ ነገሩን አስበው ፀሐይ በየቀኑ በሰማይ ላይ የምትወጣው ለአንተ ነው። አዎን ፀሐይ ! ይህ ግን ምንም አይመስለንም። ፀሐይ በየቀኑ እንደምትወጣ እናውቃለን ነገር ግን ምትወጣው ለአንተ ነው፡ ዝናብ ሲዘንብ የሚዘንበው ለአንተ ነው። እግዚአብሔር ይሄን ያህል ይወድሃል።

ኦሪት ዘዳግም 7÷9 እንዲህ ይላል፤
"አንተም አምላክህ እግዚአብሔር እርሱ አምላክ እንደ ሆነ
ለሚወዱትም ትእዛዙንም ለሚጠብቁ ቃል ኪዳኑንና ምሕረቱን
እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ የሚጠብቅ የታመነ አምላክ እንደሆነ እወቅ"።

እግዚአብሔር እንደሚወድህ ለማወቅ በሺህ የሚቆጠሩ የትውልዶችን ኪዳን እንደሚጠብቅ ማየት ያለብህ ይመስልሃልን? አየህ እግዚአብሔር የዘላለም አምላክ ነውና በአንተ የደከመና የተሰላቸ አይደለም። ብዙዎቻችን እግዚአብሔር በውድቀታችንና በበደላችን ያሰለቸነው ይመስለናል ነገር ግን ይህን ማሰብ የለብንም ፍቅር አይሰለችም እግዚአብሔርንም አትውደደን ማለት አይቻልም። ፍቅር እግዚአብሔር የሚያደርገው ሳይሆን እርሱ ራሱ ፍቅር ነው።

በዚህ ምድር ላይ የኖሩ እጅግ የዘቀጡ፣ የነቀዙና በኢየሱስም ፊት ላይ የተፉ ኃጢአተኞችን "ከአንተ ጋር አንዳች ነገር የለኝም፣ ወደ ሲኦል በመውረዴም ፍፁም ደስተኛ ነኝ" የሚሉትን እንኳ እግዚአብሔር ይወዳቸዋል። እንግዲህ እግዚአብሔር የተመረጡትንና ለእርሱም አገልግሎት የተለዩትን እንዴት አይወዳቸውም?

"ኢየሱስን እንደ ግል አዳኜ ተቀብዬዋለሁ፣ ደግሞም እወደዋለሁ" ትል ይሆናል። ነገር ግን እግዚአብሔር እንደሚወድህ ምን ያህል እርግጠኛ ነህ? በማለት ልጠይቅህ እፈልጋለሁ።

"እግዚአብሔር ይወድሃል" የሚለው ነገር በጣም ቀላል መልእክት ነው። ይሁንና እግዚአብሔር በአንተ ውስጥ የሚያስቀምጣቸውን ነገሮች በሙሉ ለመረዳት ይህ ዋንኛ መሠረት ነው።

ምንም ያህል ብትማርና የእግዚአብሔርንም ነገር የቱንም ያህል ብትመረምርና ብትፈልግ እግዚአብሔር እንደሚወድህ ካላመንህ የትም መድረስ አትችልም። እግዚአብሔር ለአንተ ያለው ፍቅር ለእምነትህ፣ ከኃጢአት ነጻ እንድትወጣና ያለፍርሃት ሌሎችን ለማገልገል እንድትችል መሠረት ነው። ለአንተ ያለውን ፍቅር ትቀበላለህን?

## እግዚአብሔር ይወድሃል!

## 2. ብቁ ነኝን?

> "ይህም ተስፋ ለእፍረት አይዳርገንም፣ እግዚአብሔር በሰጠን በመንፈስ ቅዱስ ፍቅሩን በልባችን አፍስሶአልና።"

"ገና ደካሞች ሳለን፣ ልክ ጊዜው ሲደርስ፣ ክርስቶስ ስለ ኃጢአተኞች ሞቶአልና። ለጽድቅ የሚሞት ሰው ማግኘት እጅጉን ያዳግታል፣ ለደግ ሰው ሲል ሊሞት የሚደፍር ምናልባት ይገኝ ይሆናል። ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞተ ይህም እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያሳያል"።

“አሁን በደሙ ከፀደቅን፣ ይልቁንማ በእርሱ በኩል ከእግዚአብሔር ቁጣ እንዴት አንድንም! የእግዚአብሔር ጠላቶች ሳለን በልጁ ሞት ከእርሱ ጋር ከታረቅን፣ እርቅን ካገኘን በኋላ በሕይወቱማ መዳናችን እንዴት የላቀ አይሆንም!
ሮሜ 5÷5-10 (አመት)

ብዙዎቻችን እግዚአብሔር የሚወደን ኃጢአት እስካልሠራን ድረስ ብቻ እንደሆነ ይሰማናል፡፡ ብዙ ሰዎች ራሳቸውን መቀበል ይቸገሩና እግዚአብሔር አይወደኝም ይላሉ፡፡ ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል “ታስበው ዘንድ ሰው ምንድን ነው?” (መዝ 8÷4)፡፡ እኛ የእግዚአብሔር ፍጥረታት ነን በመሆኑም ስለሚወደን ይወደናል፡፡ እርሱ ፍቅር ነው (1 ዮሐ 4÷16)

እግዚአብሔር ይወድሃል አንተ ለእርሱ ልዩ ነህ፡፡ ይህም ማለት የተለየህ ነህ፡፡ አንተ እኔን ልትሆን እኔም አንተን ልሆን ስለማልችል የተለየህ ነህ፡፡ አንዳችን ሌላውን ልንመስል ብንሞክር ምስኪኖች እንሆናለን፡፡ በዚህም ዲያብሎስ ብቁ እንዳይደለን ለመናገር አጋጣሚ ያገኛል፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ በእግዚአብሔር ዘንድ “ብቁ” መሆን አያስፈልግህም፡፡

ኢየሱስ ለአንተ የሞተው አንተ ታላቅና አስገራሚ ሰው ስለሆንህ ነው? ወይስ እርሱ ለአንተ የሞተው ስለሚወድህ ነው? መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው ኢየሱስ ለአንተ የሞተው ስለሚወድህ ከሆነ፣ በደሙ ከፀደቅህ በኋላ አሁን እንዴት አብልጦ አይወድህም? (ሮሜ 5÷8-9) እርሱ በየቀኑ የምትፈጽመውን ስህተት በሙሉ ከፍቅሩ የተነሣ ይቅር ይልሃል፡፡ እርሱ እስከ አሁኗ እለት ድረስ በኃይልና በድል እንድትደርስ ከፍቅሩ የተነሣ ይወድሃል፡፡

አንድ ቀን እግዚአብሔር ስሕተታችንንና በደላችንን እንዴት እንደሚመለከተው አሳየኝ፡፡ አንዲት ሶስትና አራት ዓመት የሚሆናት ሕፃን ልጅ እናቷ በቤት ውስጥ የምትሠራውን ሥራ ትመለከት እንደነበር እስቲ አስብ ልጂቱ እናቷን በጣም ስለምትወድ ባልዲና ቁራጭ ጨርቅ ይዛ በበረንዳው በኩል የሚገኘውንና ወደ ውጭ የሚያሳየውን መስተዋት ለመወልወል ተነሳች መስተዋቱን በሚገባ ከፈገፈገች በኋላ በጨርቅ መስተዋቱን አፀዳች፡፡

እርግጥ መስተዋቱ በውሃና በሳሙና ጭምልቅልቅ ብሏል፡፡ እናቲቱ ልጂቱ ያደረገችውን ነገር ስትመለከት ንፁህ የመስተዋት መወልወያውን ተጠቅማበታለች፣ እናም አንገቷን እንቅ ለማድረግ ይቃጣታል ልጂቱ ግን ወደ እናቷ መጥታ በሚጣፍጥ ድምጿ እንዲህ አለች፣ “እማዬ እማዬ መስተዋቱን ወ ለወልኩልሽ በደንብ አድርጌ ነው የወለወልኩት፣ እማዬ እወድሻለሁ”፡፡

ልጆን የምትወድ እናት እንዲህ አለች፣ “በእርግጥ መልካም ነገር አድርገሻል ስለረዳሽኝ አመሰግናለሁ” ከዚያም ልጂቱ ወደ ጨዋታዋ ስትሄድ የተበላሸውን ነገር ካፀዳች በኋላ ደግማ እንዲህ እንዳታደርግ ትመክራታለች፡፡

እግዚአብሔር በእኛም ሕይወት እንዲህ እንደሚያደርግ ነገረኝ፡፡ እርሱ ሁልጊዜ ቆሻሻችንን ያፀዳል፡፡ እግዚአብሔር ከአንተ የሚፈልገው ልታደርግ የምትችለውን ሁሉ ከልብህ እንድታደርግ ብቻ ነው ልታደርገው የማትችለውን እንድታደርግ ከአንተ አይጠብቅም፡፡ “እግዚአብሔር ሆይ! አንተ ልክ ነህ እኔ ተሳስቻለሁ ሞክሬ ነበር፣ ነገር ግን ልለውጠው አልቻልኩም” የምትል ከሆነ ሊለውጥህ ይችላል፡ እርሱ ይህን ማድረግ ይቻለዋል ምክንያቱም ያለ እርሱ እርዳታ ራስህን መለወጥ እንደማትችል ያውቃል፡፡

> “እግዚአብሔር መንፈሱን ሳይሰፍር ስለሚሰጥ እግዚአብሔር
> የላከው የእግዚአብሔርን ቃል ይናገራል፡፡ አብ ወልድን ይወዳል፣
> ሁሉንም ነገር በእጁ ሰጥቶታል”፡፡
>
> ዮሐንስ 3÷34-35 (አመት)

አንድ ቀን መጽሐፍ ቅዱሴን ሳጠና ይህን ጥቅስ አሰላስል ነበርና እግዚአብሔር መንፈሱን እየሰፈረ እንደማይሰጥ ስረዳ በደስታ ጮህኩ እርሱ ጥቂት ከዚህ ጥቂት ከዚያ እየሰፈረ አይሰጠንም፡፡

ይልቁንም እንዲህ ይለናል፣ “እነሆ፣ ያለኝን በሙሉ ውሰዱ”፡፡ የእግዚአብሔርን ኃይልና ፍቅር ዛሬውኑ ልትወስድ ትችላለህ፡፡ አንተ የሚያስፈልግህ ነገር በሙሉ እርሱ አለው፣ መጥተህ ከእርሱ ዘንድ እንድትወስድ ይፈልጋል፡፡ ለምን? ምክንያቱም ይወድሃል፡፡ ለመውሰድ

ጆብቁ ሆኖ መገኘት አያስፈልግህም ምክንያቱም ራስህን ብቁ ለማድረግ ፈጽሞ አትችልም፡፡ ደግሞም ብልኅና ብልጥ መሆን አያስፈልግህም፡፡ እግዚአብሔር ስለሚወድህ ሊሰጥህ ይፈልጋል፡፡

በዘዳግም 7÷6-7 ላይ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣
"አንተ ለአምላክህ ለእግዚአብሔር ቅዱስ ሕዝብ ስለሆንክ፣
አምላክህ እግዚአብሔር የራሱ ሕዝብ፣ ርስትም እንድትሆንለት
በምድር ላይ ከሚኖሩ ሕዝቦች ሁሉ መረጠህ፡፡"

"እግዚአብሔር እናንተን የወደዳችሁና የመረጣችሁ ከሌሎች
ሕዝቦች በቁጥር ስለበዛችሁ አይደለም፣ ቁጥራችሁም ከሌሎች
ሕዝቦች ሁሉ እጅግ አነስተኛ ነበር፡፡"

እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ለእርሱ የተለዩ ሕዝቦች አድርጎ መረጣቸው እኛም እንደ ቤተክርስቲያን መንፈሳዊዋ እስራኤል ነን፡፡ ስለሆነም ይህ ቃል ለእነርሱ እንደተሰጠ ሁሉ ለአንተም ተሰጥቷል እግዚአብሔር እንዲህ አላቸው "የመረጥኳችሁ ቁጥራችሁ በምድር ላይ ከሚኖሩ ነገዶች ሁሉ ስለሚበልጥ አይደለም"፡፡ ይህን ከእኛ ጋር ስናዛምደው እንዲህ ማለት ነው፣ "የመረጥኳችሁ ሁሉንም ነገር በትክክል ስላደረጋችሁ ወይም አስገራሚ ሰዎች ስለሆናችሁ አይደለም"፡፡

ከዚያም ከሌሎች ሕዝቦች ይልቅ በቁጥር በጣም አናሳ እንደሆኑ ይናገራል፡፡ ከመዳንህ በፊት ከሁሉ ይልቅ ኃጢአተኛ ነበርኩ ብለህ ሳታስብ አትቀርም፡፡

ይሁንና በቁጥር 8 ላይ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል
"ነገር ግን እናንተን በብርቱ እጅ ያወጣችሁ፣ ከባርነት ምድርና ከግብጽ ንጉስ ፈርኦን መዳፍ የተቤዣችሁ እግዚአብሔር እናንተን ስለወደዳችሁና ለአባቶቻችሁ የማለላቸውን

ይህ ታላቅ መልእክት ነው! እግዚአብሔር "ፍቅሬን በላያችሁ አደረግሁ፣ ቅዱሳንም እንደሆናችሁ ነገርኳችሁ፡፡ ልዩ እንደሆናችሁ ነገርኳችሁ፡፡ የመረጥኳችሁ መልካምና አስገራሚ ሰው ስለሆናችሁ ሳይሆን ስለወደድኳችሁ ነው" አለ፡፡ እግዚአብሔር ዛሬ ምን ማድረግ እንዳለባችሁ እንደሚፈልግ ታውቃላችሁ? ፍቅሩን እንድትቀበሉና እንድትወስዱ ይፈልጋል፡፡

ራሳችንን አለመቀበል የብዙዎቻችን ችግር ነው እግዚአብሔር እንደሚወደን አምነቱ የለንም ወይንም ሰዎች አይወዱንም እንላለን፡፡ “ሰዎች እንዴት ሊወዱኝ ይችላሉ? እኔ የማልጠቅም ሰው ነኝ” እንላለን፡፡ የማልጠቅምና የማልረባ ሰው ነኝ ብለህ የምታስብ ከሆነ ከሁሉ ምስኪንና ረብ የሌለው ህይወት እየኖርክ ነው፡፡ ስለዚህም በውስጥህ ካለው አመለካከት ልቀህ ወይንም አይለህ መኖር አትችልም፡፡

የእኔ ትልቁ ችግሬ ራሴን መቀበል አለመቻሌ ነው፣ 75 በመቶ የሚሆነውን ጊዜዬን የማሳልፈው ራሴን ለመለወጥ በመጣር ነው፡፡ ብዙ ስለተናገርሁ አሁን ዝም ማለት አለብኝ እላለሁ በኂላ ግን ዝም ካልሁ በሐዘን እሞላለሁ፣ ሰዎች ሁሉ ለምን ዝም እንዳልሁ ለማወቅ ይፈልጋሉ ከዚያም እንዲህ ብዬ አሰብሁ፣ ለፍላፊ እንደሆንሁ ነገርሽኝ፣ አሁን ተወኝ፣ ዝም ለማለት እየሞከርሁ ነኝ፡፡

በዚህ ችግር ውስጥ ለምን ያህል ዓመት እንዳለፍሁ ልነግርህ አልችልም አሁንም ቢሆን የማውራት ችግር አለብኝ፡፡ ብዙ የሚናገሩ ሰዎች ያገቡት ዝምተኛ ሰዎችን ነው፡፡ ይህ ደግሞ ብዙ ተናጋሪ መሆናችንን ያጎላዋል፡፡ ዲያብሎስም ድካማችንን እያስታወሰ ይወቅሰናል፡፡ ይህ “ኩነኔ” ይባላል፡፡

እግዚአብሔር ከኩነኔ ነጻ እንድንወጣ ይፈልጋል፣ ይሁንና ነጻ ለመውጣት እምነትና ድፍረት ያስፈልጋል፡፡ ምንም ያህል የበደለኝነት ስሜት ቢሰማህ ለፈፀምኸው በደል አንዳች ነገር እንደማይፈይድ ታውቃለህን? አንድ በደል ስትፈጽም እግዚአብሔር ይወደኛል ብለህ ለማመን እጅግ ሊከብድህ ይችላል፡፡

ዲያብሎስ ምን ያህል በደለኛ፣ ከንቱና ለምንም የማንጠቅም እንደሆንን አሁንም አሁንም ሊነግረን ይፈልጋል፡፡ “አሁንም በደል ሠራህ” ይለናል፡ “ለመሆኑ አንተ ማን ነህ? አንተ ምንም የማትጠቅም በደለኛ ሰው እግዚአብሔር እንደሆነ አይባርክህም አሁን ለመመስከር አትችልም ምንም ነገር ልታደርግ አትችልም” ይለናል፡፡

አሁን ነው በውስጥ ሰውነትህ ቆመህ በድፍረት እንዲህ ማለት የሚገባህ፣ "አባት ሆይ በድያለሁ በኢየሱስ ደም ይቅር እንድትለኝ እጠይቃለሁ ይህን የምጠይቅህ ከልቤ ነው ይቅርታህን እሻለሁ ዲያብሎስ አሳብህ አይሳካም ኢየሱስ የኃጢአቴን እዳ ከፍሎአል አንተን ምንም አይመለከትህም" ከዚያም በሰላም መሄድና ደስ መሰኘት ትችላለህሆኖም "ይህን መጥፎ ነገር በተደጋጋሚ አደርጋለሁ" ብለህ ታስብ ይሆናል እኔም በዚህ ነገር ራሴን መውቀስ እስካቆምሁበት ጊዜ ድረስ እንዲሁ አስብ ነበር፡፡ በሰራኸው ነገር ራስህን መውቀስ ስታቆም፣ ያን ነገር ማድረግ ታቆማለህ፡፡

በደልና ኩነኔ ነጻ ሰው እንዳትሆን ወደታች ይቀብርሃል፣ በሐዘን እንድትሞላ ያደርግሃል የማይኮነን ሰው ለመሆን ድፍረት ይጠይቃል ደፋር ሰው መሆን አለብህ ደግሞም በእምነት መቆምና በደልንም ወግድ ማለት አለብህ፡፡ ዲያብሎስ እንዲህ ሊልህ ይችላል፣ "እንዲህ ስትል በሆነው ነገር ምንም አላዝንም ማለትህ ነው? ለምን? ቢያንስ ለጥቂት ሰዓታት ልታዝን ይገባህ ነበር፣ በእውነቱ መጥፎ ነገር አድርገሃል"፡፡ አንተ ግን እንዲህ ብለህ መልስለት፡ "የለም ምንም ሐዘን አይሰማኝም፣ በሆነው ነገር ምንም አላዝንም" በመጀመሪያ እንዲህ ብሎ መናገር ከባድ ነው ሆኖም ሶስት አራት ጊዜ ደጋግመህ ከተናገርህ እንዴት መመለስ እንደሚገባህ ታውቃለህ፡፡

በትንቢተ ኢሳይያስ ምዕ 53 ቁጥር 5-6 እና 11 ላይ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገረው ኢየሱስ ኃጢአታችንን ሲሸከም፣ ኩነኔያችንንም ተሸክሞአል፡፡ ዲያብሎስ ከኩነኔያችን ነጻ እንድንወጣ አይፈልግም ለምን? ምክንያቱም በኩነኔ ስር ካለህ በእግዚአብሔር ፍቅር ደስ መሰኘት አትችልም፣ ኩነኔ ከእግዚአብሔር ይለይሃል፣ በአንተና በእግዚአብሔር መካከል እንደ ብረት ግድግዳ ይቆማል፡፡ በኩነኔ ስር ካለህ እግዚአብሔር አብን ማየት አትችልም የምታየው የራስህን በደልና ኃጢአት ብቻ ነው፡፡

ከኩነኔ ነጻ ወጥተህ ተመላለስ እግዚአብሔር ፀጋዬ ኃጢአትህን ለመሸን በቂ ነው ካለህ የተናገረውን ነገር እመን፡፡ እርሱ ይወድሃል ፀጋውና ይቅርታው ነጻ ስጦታ ናቸው፡፡ ዛሬውኑ ተቀበላቸው!

# እግዚአብሔር ይወድሃል!

## 3. ፍቅር ኅብረት ነው

“እኛም እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር አውቀናል
አምነንማል እግዚአብሔር ፍቅር ነው በፍቅር የሚኖር
በእግዚአብሔር ይኖራል እግዚአብሔርም በእርሱ ይኖራል”፡፡
1ዮሐ 4÷16

የእግዚአብሔርን ፍቅር እንዴት መረዳትና መገንዘብ ትችላለህ? እግዚአብሔር የቱንም ያህል ቢወድህ ለፍቅሩ መረዳት ከሌለህ ጥቅም የለውም፡፡ አንድ ሰው እንደሚወድህ ቢነግርህ እጅግ ደስ ትሰኛለህ የሚወድህ ሰው እንዳለ ስታውቅ ደስ ይልሃል፡፡ እግዚአብሔር ይወድሃል ፍቅሩን ሊያሳይህ ይፈልጋል፡፡ በየቀኑም ከእርሱ ጋር ህብረት እንድታደርግ ይፈልጋል፡፡

ከእግዚአብሔር ጋር የግል ኅብረት አለህ? ከብዙ ጊዜ በፊት ስላዳነህ ብቻ ከእግዚአብሔር ጋር መልካም ኅብረት አለህ ማለት አይቻልም፡፡ ዛሬ ጠዋት ዐይኔን ስገልጥ በመጀመሪያ የማስበው ስለ እግዚአብሔር ነው እንዲሁም ሲመሽ ወደ መኝታዬ ስሄድ በመጨረሻ የማስበው ስለ እግዚአብሔር ነው፡፡ ደግሞም በቀን ውሎዬ ሁሉ የማስበው ስለ እግዚአብሔር ነው፡፡ በዚህ ትልቅ ዓለም አምላኬን ከማገልገልና እርሱንም ደስ ከማሰኘት ውጪ ሌላ ምኞት የለኝም፡፡ ይህ በምንም የማይተካ ታላቅ ነገር ነው፣ ይህንንም ለማግኘት ሌላውን ሁሉ መተው ያስፈልጋል፡፡

በእያንዳንዳችን ውስጥ እግዚአብሔር ብቻ ሊሞላው የሚችል አምላክ ሠራሽ ክፍተት አለ፡፡ የምንሮጥለት የትኛውም ነገርና ምኞት ሊሞላው አይችልም፡፡ ለራስህ እንዲህ ትል ይሆናል፣ “ይህን አስቀድሜ አውቀዋለሁ ኢየሱስንም ተቀብያለሁ”፡፡ ይሁንና በየደቂቃው፣ በየቀኑና በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ትቀበለዋለህን? የእግዚአብሔርን ፍቅር ትቀበላለህን?

እግዚአብሔር እጅግ ይወድሃል ለእርሱም ልዩ ነህ እግዚአብሔር የፈጠረን ከእርሱ ጋር ኅብረት እንድናደርግ መሆኑ ለአንተ ታላቅ ዓላማና ፍፁም ፈቃድ እንዳለው ያሳያል፡፡

አንድ ጓደኛዬ አንድ ጊዜ ስትፀልይ ራእይ አየች፡፡ እግዚአብሔር አብ ጠዋት ከመኝታቸው ሲነሱ ወደ አሜሪካን ሕዝቦች ቤት ሲሄድ አየች ወደ ሁሉም ቤት የሄደው ከእነርሱ ጋር ህብረት ሊያደርግና ሊነጋገር ነበር፡፡ ወንበር ሳብ አደረገና ተቀመጠ ሰዎቹ ከየመኝታቸው ተነሱ መጡ ሄዱ፡፡ ደግሞም መጡ ሄዱ፡፡ እግዚአብሔርንም “እግዚአብሔር ሆይ፣ በኋላ እናነጋግርሃለን ለጥቂት ጊዜ በዚያው ሆነህ ታገሰን፡፡ ይህን እንደጨረስሁ አነጋግርሃለሁ፡፡ እግዚአብሔር ሆይ በኋላ ኅብረት እናደርጋለን በኋላ ፡እግዚአብሔር በኋላ እግዚአብሔር”፡፡

ቀኑ መሸ ይህን ራእይ ያየችው ልጅ ልቧ እንደተሰበረ ተናገረች ምክንያቱም እግዚአብሔር ከተከሻው አቀርቅሮ ከቤት ወጥቶ ሲሄድ አየችው በዚያን ቀን ከእርሱ ጋር ለመነጋገር አንድም ሰው አልመጣም ነበር፡፡

ከልክ በላይ በሥራ ተጠምደህ አትዋል፡፡ የምትፀልይበትና ከእግዚአብሔርም ጋር ኅብረት የምታደርግበት ጊዜ ከሌለህ ከልክ በላይ በሥራ ተጠምደሃል ማለት ነው፡፡ጊዜ ወስደህ እግዚአብሔርን እንደምትወደው ንገረው፡፡ ሁሉም ነገር ያልፋል የማያልፈው እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ እውነታው ይህ ነው እንግዲህ ከእርሱ ጋር ኅብረት ከሌለህ ከእርሱ ጋር ኅብረት ለማድረግ ትንሽ ጊዜው ሊያልፍብህ ይችል ይሆናል፡፡ እንዲህ ሲባል ግን ወደ መንግስተ ሰማይ አትገባም ማለት አይደለም ሆኖም የድል ሕይወት በመኖር የሚገኘውን ደስታ ሳታይ ታልፋለህ፡፡

የእግዚአብሔርን ፍቅር የምታጣጥምበት የቀጠሮ ቀን እንዲኖርህ እመክርሃለሁ፡፡ የእግዚአብሔር ሰው ወይም ሴት ለመሆን በእምነትና በጌታ እንጂ በራስ መደገፍን አቁም፡፡ ተመልሰህ እንደ ሕፃን ልጅ በመሆን በአባትህ በእግዚአብሔር እግር ስር ተጫወት ፍቅሩን እንዲገልጥልህ ፍቀድለት፡፡ እስክትፈቅድለት ድረስ አንተም ፍቅርህን ልትገለጥ አትችልም፡፡

1 ዮሐንስ 4÷16 እንዲህ ይላል፣
"እኛም እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር አውቀናል፣ አምነንማል።..."

በዚህ ማለዳ ተነስተህ እግዚአብሔር ምን ያህል እንደሚወድህ ለማሰብ ከእርሱ ጋር ጊዜ ትወስዳለህን? ጠዋት ከመኝታህ ስትነሳ ምንም የምታደርገው ነገር ያለ አይመስልህም። ይሁንና ስጋህን ለማንቃትና መንፈሳዊ ሰውነትህን አዘጋጅተህ ማድረግ የሚገባህን መልካም ነገሮች ለማድረግ አንደበትህን መጠቀም አለብህ።

ስለሆነም ጠዋት ከመኝታህ ስትነሳ እንዲህ በማለት ጀምር፣ "አባት ሆይ በጣም ስለምትወደኝ አመሰግንሃለሁ። ኢየሱስ ለእኔ እንዲሞት ስለላክኸው አመሰግንሃለሁ። የትንሣኤው ኃይል በውስጤ ስለሚኖር አመሰግንሃለሁ" ጌታ ሆይ ዛሬ በምሄድበት ስፍራ ሁሉ ለበረከት ስለምታደርገኝ አመሰግንሃለሁ። እግዚአብሔር ሆይ ትወደኛለህ ትወደኛለህ በዚህች ቤቴ ውስጥ እንዳለሁ ትወደኛለህ። እኔ ልዩ ልጅህ ነኝ የዐይንህ ብሌን ነኝ ትወደኛለህ!

በእግዚአብሔር ፍቅር እንደተከበብህና እንደተሸፈንህ መገንዘብህን ተረዳ።መጽሐፍ ቅዱስ በኢሳይያስ 49÷16 እግዚአብሔር በእጁ መዳፍ እያንዳንዳችንን እንደቀረጸን እወቅ።

እግዚአብሔር ምን ሊለን እንደሚወድ ለመግለጽ አዳጋች ቢሆንብኝም ነገር ግን "እስቲ ተመልከቷቸው?" "ውብ አይደሉም?" "በጣም እወዳቸዋለሁ" የሚል ይመስለኛል። ለአንተም እንዲሁ ይወድሃል ከአንተም ጋር ኅብረት ለማድረግ እንደሚናፍቅ ሊነግርህ ይወዳል።

እግዚአብሔርን የምታመሰግንና ከእርሱም ጋር ያለህን ኅብረት ልታሳድግ እንደሚገባህ አስብ። አንዳንድ ጊዜ በፀሎት በፊትህ ተደፍተህ እግዚአብሔርን ስለ ማዳኑ ልታመሰግነው ይገባል። እግዚአብሔርን ከማሳዘን ተመልሰህ ውደደው። በ1ዮሐንስ 4÷16-17 ላይ እንዲህ የሚለውን ቃል አንብብ።

"…እግዚአብሔር ፍቅር ነው፣ በፍቅር የሚኖር በእግዚአብሔር ይኖራል፣ እግዚአብሔርም በእርሱ ይኖራል።

"በፍርድ ቀን ድፍረት ይሆንልን ዘንድ ፍቅር በዚህ ከእኛ ጋር ተፈጽሚል"።

እግዚአብሔር እንደሚወድህ ስታውቅ በእርሱ መደገፍና በታማኝነቱም መታመን ትጀምራለህ።

የበረከት ምንጭ የእግዚአብሔር እኛን መውደድ ነው። በረከታችንም እምነት ኃጢአትን ድል መንሣት ብልጽግና ደስታና ሌሎችም ናቸው እነዚህን የምናገኘው እርሱ እኛን እንዲወደን ስንፈቅድለት ነው። ብዙውን ጊዜ ነገሩን በመገልበጥ "እግዚአብሔርን መውደድ አለብኝ" ብለን እናስባለን። እኔ እንደማምነው በመጀመሪያ እግዚአብሔር እንዲወድህ መፍቀድ አለብህ። እግዚአብሔር እንዲወድህ እስከምትፈቅድለት ድረስ ለእግዚአብሔር ያለህን ፍቅር ለመግለጽ ትችላለህ ብዬ አላምንም።

ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ማድረግ እንዳለብህና በእርግጥም ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ማድረግ እንደሚያስፈልግህ ልነግርህ እችላለሁ ነገር ግን ይህን የምታደርገው እንዴት ነው? እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ኅብረት ማድረግ እንዳለብኝ ሲነግረኝ ሶፋ ወንበሬን አመጣሁና ተቀመጥሁ ከዚያም "እግዚአብሔር ሆይ ምን ልትለኝ ትአልጋለህ?" አልሁት። ይህ ትክክል ነው! ከእግዚአብሔር ጋር እንዴት ኅብረት ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም ምክንያቱም በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር ምን ያህል እንደሚወደኝ አላውቅም ነበር።

ለሰዎች ያለህን ስሜት የምትገልፀው እንዴት ነው? እንደሚወዱህ ሳታውቅ እወዳችኋለሁ፣ አከብራችኋለሁ ትላቸዋለህ? እንዲህ ብል ሰዎች እንደ ሞኝ ይቆጥሩኛል ብለህ ትፈራለህ። እንደሚወዱህና እንደሚቀበሉህ የምታውቃቸው ሰዎች ናቸው ምቾት የሚሰጡህ። ከማንም ሰው ጋር የማላደርገውንና የማልነጋገረውን ነገር ከባለቤቴ ጋር አደርጋለሁ ምክንያቱም ባለቤቴ እንደሚወደኝ አውቃለሁ። እግዚአብሔርንም አስመልክቶ ልክ እንደዚሁ ነው።

ተነሣና አንድ እርምጃ ተራመድ ለእግዚአብሔር እድል ስጠው፣ ከእርሱ ጋር እንዴት ኅብረት እንደምታደርግ ያስተምርሃል፡፡ ራስህን እንዲህ ብለህ ጠይቅ፣ "እግዚአብሔር ምቾት ይሰጠኛል?"

## እግዚአብሔር ይወድሃል!

# 4. ፍቅር መታመንና እምነት

"በክርስቶስ ኢየሱስ ሆኖ በፍቅር የሚሠራ እምነት እንጂ መገረዝ ቢሆን ወይም አለመገረዝ አይጠቅምምና"፡፡
ገላትያ 5÷6

እምነት እንዲኖረን ብዙዎቻችን ስንጥር እንታያለን፡፡ በእርግጥም ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አንችልም (ዕብ 11፡6)፡፡ ስለዚህም ብዙ እምነት እንዲኖረን እንጥራለን፡፡ እውነታውም እምነት የሚነሣው ከልብ ነው፡፡ የምናገኘውም ከእግዚአብሔር ጋር በሚኖረን የፍቅር ኅብረት ብቻ ነው፡፡ እምነትን ላስተምርህ ባልችልም የእምነትን መርህ እንድትረዳና ረሀብ በውስጥህ እንዲኖር ላደርግ እችላለሁ፡፡ እምነት የሚገኘው ከእግዚአብሔር መገለጥ ብቻ ነው፡፡

እምነት በራስህ ጥረት ለማግኘት የምታደርገውን ሙከራ አቁመህ እግዚአብሔርን ደስ አሰኝ፣ ይህን ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ለማድግና እርሱን ለመውደድ አውለው፡፡ ቀኑን በሙሉ እርሱን በመውደድና በመፍቀድዋል፡፡

"በእምነት እንጂ በማየት አንመላለስምና"
2ቆሮ 5÷7

አንድ ጊዜ ይህን ክፍል ሳነብ እግዚአብሔር ለልቤ አንድ ብርቱ ነገር መናገር ጀመረ፡፡ በእምነት ለመመላለስ እየሞከርሁ ነበር፡፡ በሕይወቴ በማንኛውም አቅጣጫ በእምነት ለመመላለስ

እፈልግ ነበር። በሌላ አነጋገር ከእግዚአብሔር ጋር ባለኝ ኅብረት መሠረት በእምነት እመላለስ ነበር። ይህ ምን ማለት እንደሆነ ተረዳህ? ጻድቅ አይደለሁም ብሎ የሚያስብ ሰው በእምነት መመላለስ እንዳለበት ሊዘነጋ ይችላል። እንዲሁም እኔ ምንም የማልጠቅም አፈር ነኝ፣ እግዚአብሔርም አይወደኝም ብሎ የሚያስብ ሰው በእምነት መመላለስ እንዳለበት ሊዘነጋ ይችላል። ብዙ ሰዎች በእምነት ለመመላለስ ይሞክራሉ፣ ይሁንና በልባቸው ውስጥ እነዚህ ነገሮች የሉም።

ገላትያ 5-6 ላይ እንደምናነበው እምነት የሚሰራው በፍቅር ነው። እግዚአብሔር አንድ ሃሳብን በልቤ አኖረ፣ "ብዙ ሰዎች ልክ እንደዚሁ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ሰዎችን ካልወደድን እምነታችን አይሰራም" ብለው ያስባሉ። ነገር ግን ምንባቡ ይህን አይነግረንም። ምንባቡ የሚያስተምረው እንደምወዳቸው ካላወቁ እምነታቸው አይሰራም የሚል ነው"። እምነት ያለ ፍቅር ስራ የለውም። ሰዎችን መውደድ የአንተ ችሎታ አይደለም። ቁም ነገሩ ሁሉን ቻዩን እግዚአብሔር እንዲወድህ መፍቀድህ ነው።

ይህ ትልቅ ልዩነት አለው። እግዚአብሔርን መታመንና በእምነት መመላለስ፣ እርሱን መደገፍና በነገር ሁሉ እርሱን መታመን ነው። አንድ ሰው እንደሚወድህ ካላወቅህ እንዲህ ማድረግ አትችልም። ደግሞም ልትዘነጋው ትችላለህ፤ እግዚአብሔር እንደሚወድህ ካላወቅህ እርሱን ልትታመንበት ከቶ አትችልም።

እግዚአብሔር ምን ያህል እንደሚወድህ ካወቅህ፣ ፈውስ ለመቀበል እምብዛም ከባድ አይሆንብህም። ደግሞም የገንዘብ ጥያቄዬ ይሟላ ይሆን ብለህ እምብዛም አትጨነቅም።

ፍላጎትህን የማትቀበልበት ምክንያት እግዚአብሔር እንደሚሰጥህ በእርግጠኝነት ስለማታምን ነው። ምናልባት "ማመን እፈልጋለሁ"፤ ነገር ግን እንዴት ማመን እንደምችል አላውቅም" ትል ይሆናል።

በውስጥህ የእግዚአብሔር ፍቅር አለ፤ አሁን ማድረግ ያለብህ እግዚአብሔር የሚያሳይህን ነገር ለመቀበል መዘጋጀት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል...

“እርሱ አስቀድሞ ወዶናልና እኛ እንወደዋለን” (1ዮሐ 4÷19)። እግዚአብሔር አስቀድሞ እንደወደደህ እርግጠኛ ካልሆንህ እግዚአብሔርን ለመውደድ ከባድ ይሆንብሃል።

ሁሉም ነገር በልብህና በውስጥህ ነው። ሁሉም ነገር በዚያ ውስጥ አለ! እግዚአብሔር ይወድሃል! አንተ ድንቅ እና ውብ ሰው ነህ! በዚህ ዓለም ስትኖር እግዚአብሔር እንደሚወድህ ያህል ማንም ሰው ሊወድህ አይችልም።

ከእግዚአብሔር በቀር ሌላ ማንም አያስፈልግህም፤ ይሁንና እርሱ ሌሎች ሰዎችን በሕይወትህ ይሰጠሃል። እውነታው ሌሎች ሰዎች ባይኖሩም ነገር ግን አንተና እግዚአብሔር ብቻ ብትሆኑ ምንም አይጎድልብህም። እግዚአብሔር መልካም ወዳጅህ ይሆናል። ጓደኛ ከሌለህ እርሱ ጓደኛ ይሆንሃል። አባትና እናት ከሌለህ እርሱ አባትም እናትም ይሆንሃል።

እግዚአብሔር ይሄን ያህል ይወድሃል። ለዚህም ነው ለሚያስፈልግህ ነገር በሙሉ በእርሱ መታመን ያለብህ። እርሱ በጣም ስለሚወድህ የሚያስፈልግህን ነገር በሙሉ ይሰጥሃል። እግዚአብሔር እንደሚሰጥህ እስካላወቅህ ድረስ ከእርሱ ለመቀበል በቂ እምነት አይኖርህም።

እምነት የሚሰራውና የሚንቀሳቀሰው እግዚአብሔር እንደሚወድህ ለማወቅ ስትፈቅድ ነው። እምነት ሰዎችን ስለወደድህና ችሎታ ስላለህ አይሰራም። አስቀድሞ እግዚአብሔር እንዲወድህ ፍቀድለት፤ ከዚያም እግዚአብሔርን እንዲህ በለው “እግዚአብሔር ሆይ እንደምትወደኝ አውቃለሁ። ሃሌሉያ! አባት ሆይ አመሰግናለሁ። ስምህን ከፍ ከፍ አደርጋለሁ”።

ስሚዝ ዊግልስዎርዝ ታላቁ የእግዚአብሔር ሐዋርያ ነው። አንድ ሰው ረጅም ሰዓት ትጸልያለህ ወይ ብሎ ጠየቀው እርሱም እንዲህ ሲል መለሰለት ከ30 ደቂቃ በላይ ጸልዬ እንደሆነ አላውቅም ነገር ግን 30 ደቂቃ ሳልጸልይ የቀረሁበት ጊዜ እንዳለ አላስታወስም አንድ ጊዜ ሲናገር ከእግዚአብሔር ጋር ሳይነጋገር ከ15 ደቂቃ በላይ ከወሰደ ንሰሐ መግባት አለብኝ ብሎ ነበር።

ነገሮችን ለማከናወን የምንሞክረው ከተሳሳተ መነሻ ነው። በራስህ ጥረት ልታከናውነው አትችልም። እግዚአብሔር የሚባርክህ ስለሚወድህ ነው። ደህንነትን እንደሰጠህ ሁሉ የሚያስፈልግህንም ነገር ይሰጥሃል።

ቤተሰቦችህ ወይም ሌሎች ሰዎች እንዲድኑ አንተ ምንም የምታደርገው ነገር የለም። እግዚአብሄር እንዲወድህ ፍቀድለት። ከዚያም ቤተሰቦችህን ስታያቸው እነርሱን መውደድ ትጀምራለህ። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገረው የምትወዳቸው ከሆነ በምትነግራቸውና በምታደርጋቸው ነገሮች እነርሱን ለማሸነፍ የምታደርገውን ሙከራ አቁመህ ወደ ኢየሱስ አመልክታቸው። የእግዚአብሔር መንፈስ ቤተሰቦችህን በፍቅሩ አማካይነት ይስባቸዋል። ነገር ግን እግዚአብሄር እንዲወድህ ካልፈቀድክለት ሌሎችን መውደድ አትችልም ። ኤፌሶን 2÷8 እንዲህ ይላል "ጸጋው ... አድኖአችኋልና"። ለመዳን ምንም ነገር እንዳላደረግህ ታስተውላለህ? ብዙዎቻችን ኢየሱስ እኛን ከማዳኑ በፊት በእጅጉ የዘቀጠን ስዎች ነበርን፤ በመሆኑም መዳናችን በእኛ ጥረትና ችሎታ ላይ የተመሰረተ አይደለም። የዳነው በአንድ ነገር ብቻ ነው፤ ይኸውም የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጠን ድረስ በእጅጉ ስለወደደን ነው (ዮሐ 3÷16)።

ጸጋ እግዚአብሔር ፍላጎታችንን ሲሞላ ለህይወታችን የሰጠን የኃይሉና የፈቃደኝነቱ መገለጫ ነው። እግዚአብሔር ድነትን እንድናገኝ እምነትን ከጸጋው የተነሳ እንደሰጠን እንዲሁ ፈውስን ለመቀበል እንድናምን እምነትን ይሰጠናል። እርሱ እረኛችን መሆኑን እናምን ዘንድ እምነትን ይሰጠናል።

መዳንን እናገኝ ዘንድ በውስጣችን ያስቀመጠው እምነት ከሃጢአታችን ሁሉ ሊያድነን የሚችል ከሆነ ይሄው በውስጣችን ያለው እምነት በህይወታችን የሚያስፈልገንን ነገር ለመቀበል ያስችለናል። እግዚአብሄር እንደሚወድህ የምታምንና እንደሚወድህም ለማወቅ የምትሻ ከሆነ፤ እርሱን በእርግጥ መታመን ትጀምራለህ። የእግዚአብሔርም ቃል እውነተኛነት መቀበል ትጀምራለህ። እርሱ ከቶ እንደማይዋሽህ ታውቃለህ፤ ምክንያቱም እርሱ ይወድሃል።

እምነት ማለት በእግዚአብሔር መታመንና መደገፍ ማለት ነው፡፡ ደግሞም በእርሱ ኀይል፣ ጥበብና መልካምነት ላይ ራስን መጣል ማለት ነው (ቆላ 1፡4)፡፡ እግዚአብሔር እንዲወድህ ስትፈቅድለት እርሱን መውደድና መታመን ማለት እንደሆነ ትማራለህ፤ ደግሞም እምነት ይኖርሃል፡፡

## እግዚአብሔር ይወድሃል!

## 5. ከፍርሃት ነጻ መሆን

> "ፍጹም ፍቅር ፍርሃትን አውጥቶ ይጥላል እንጂ በፍቅር ፍርሃት ቅጣት አለውና፤ የሚፈራም ሰው ፍቅሩ ፍጹም አይደለም"፡፡

ብዙውን ጊዜ እግዚአብሔር እንደሚወደንና በእርሱ እንደምንታመን እያወቅን እርምጃ ግን አይኖረንም ስለዚህ ድንገተኛ ነገር ህይወታችንን ሲይዘን ግራ እንጋባለን፡፡

እምነታችንን የሚሰርቅብን ጠላትና ሁኔታዎች ናቸው፡፡ በእኛ ላይ የሚገኘውን ገጠመኞቻችንን እምነታችንን ይሰርቁብናል፡፡ በህይወትህ በሚገጥምህ ሁኔታዎች እግዚአብሔር እንደማይወድህ ሊመስልህ ይችላል ስለዚህም እግዚአብሔር እንደሚወድህ ለማመን ትቸገራለህ፡፡

ከዚያም ዲያብሎስ ነጻ ካወጣህ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለይህ ፍርሃትንና ኩነኔን ይዞ ይመጣል፡፡ ከዚያም "ይህ የደረሰብህ ነገር ምንድን ነው? ይልሃል፡፡ "እግዚአብሔር የሚወድህ መስሎኝ ነበር፡፡ ታዲያ ይህ መጥፎ ነገር በአንተ ላይ የደረሰው ለምንድን ነው? ክፉ ነገር ሳታደርግ አልቀረህም፡፡ እግዚአብሔር በእርግጥ ተቆጥቶሃል"፡፡

በዚህ ሁኔታ ውስጥ በእግዚአብሔር ላይ ያለህን መደገፍና እምነትህን ማጣት ትጀምራለህ፤ እምነትህ ማነስ ሲጀምር ከእግዚአብሔር ዘንድ እርዳታ ለመቀበል ትቸገራለህ፡፡

እግዚአብሔር እንደሚወድህ ካልተረዳህ በእግዚአብሄር ላይ ሙሉ እምነት ሊኖርህ አይችልም። የዲያቢሎስን ኩነኔና ክስ ካስተናገድህ፣ እግዚአብሔር ፍቅር ይሸፈንብሀል።

1ዮሐንስ 4÷18 እጅግ ብርቱ ቃል ይናገራል፤ "ፍጹም ፍቅር ፍርሃትን አውጥቶ ይጥላል"። ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ምን እንደሚል ለማወቅ መልሼ መላልሼ አሰላስል ነበር፤ አንድ ቀን እግዚአብሔር ለመንፈሴ እንዲህ ብሎ ተናገረኝ፤ ፍጹም ፍቅር ፍርሃትን ያስወግዳል፤ እግዚአብሔር ደግሞ ፍጹም ፍቅር ነው። ይህ ፍጹም ፍቅር ነው ለአንተም እንደተሰጠ ስትገነዘብ ፤ በዚህ ዓለም ውስጥ የምትፈራው ምንም አይነት ነገር አይኖርም። እግዚአብሄር እንደሚወድህ ግላዊ መገለጥ ካለህ የምትፈራው ነገር ሊኖር አይችልም።

እግዚአብሄር እንደሚወድህ ካወቅህ እወድቃለሁ ብለህ ከቶ አትፈራም። በእግዚአብሄር የምታምን ከሆነ አትወድቅም። የምትወድቀቅ በራስህ የታመንህ እንደሆነ ብቻ ነው ። እግዚአብሄር እንደሚወድህ ካወቅህ ተቃውሞን አትፈራም።

የእግዚአብሄር ፍቅር እጅግ ብርቱ ስለሆነ ሁሉንም ነገር ይሸፍናል። ያዳነህና ነጻ ያወጣህ አምላክ ይኮንነኛል ብለህ ታስባለህ? ሰይጣን ነው የሚኮንነው። እግዚአብሄር በህይወትህ ውስጥ ባለው ሃጢአት በመውቀስ መውጫ መንገዱን ያሳይሃል። ዲያብሎስ ግን ይኮንንህና መውጫ መንገድ የለም ይልሃል።

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል
"ፍጹም ፍቅር ፍርሃትን አውጥቶ ይጥላል
እንጂ በፍቅር ፍርሃት የለም ፍርሃት
ከቅጣት ጋር የተያያዘ ስለሆነ የሚፈራ ሰው
ፍቅሩ ፍጹም አይደለም "
1ዮሐንስ 4÷18 (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

ብዙ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ሲል ከልብህ የምትወደኝ ከሆነ አትፈራኝም ወይም አንድን ሰው ከልብህ የምትወደው ከሆነ ፍርሃት ከሕይወትህ ይወገዳል ማለቱ ነው ይላሉ። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ የሚለው እንዲህ አይደለም።

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረን እግዚአብሔር እንዲወድህ ከፈቀድህለት ፍርሀት አይነግስብህም። በሕይወትህ ፍርሃት እንዳይገዛህ ከፈለግህ እግዚአብሔር እንዲወድህ ፍቀድለት። በእምነት የእግዚአብሔርን ፍቅር አሁን ተቀበል። ለመቀበልም እርምጃ ውሰድ። እግዚአብሔር ለአንተ ያለውን ፍቅር በእምነት ተቀበል።

የእግዚአብሄር ፍቅር ፍርሃትን አውጥቶ እንደሚጥል መገለጡን ከሰጠኝ በኋላ በህይወቴ መተግበር ነበረብኝ። አንድ ጊዜ መኪናችን ተበላሽቶ ትልቅ ችግር ገጠመን ። መኪናችንን ለማስጠገን ከመቶ እስከ አምስት መቶ ዶላር ያስፈልጋል እኛ ደግሞ ገንዘብ አልነበረንም ፤ ስለዚህ ዝም ብለን መኪናውን መንዳት ቀጠልን ።

አንድ ቀን ጠዋት እግዚአብሄር ለልቤ እንዲህ ሲል ተናገረኝ "ጆይስ ቀኑን ሙሉ ውደጂኝ" እኔም እንድወድሽ ፍቀጂልኝ። ምንም የምታደርጊው ነገር የለም ታላቅ እምነት ያላት ሴት መሆንም የለብሽም ብቻ ቀኑን ሙሉ ውደጂኝ እኔም እንድወድሽ ፍቀጂልኝ። ሁልጊዜ ይህን አድርጊ። ልውደድሽ!

አንድ ቀን እንደተለመደው ከእግዚአብሄር ጋር እምነቴን ለማነጽ፤ እግዚአብሄርን እያከበርኩ ህብረት አደርግ ነበር። ከዚያም ድንገት የባለቤቴን መኪና ከምናቆምበት ጋራዥ ውስጥ ሰማሁ። ባለቤቴ ከ45 ደቂቃ በፊት ወደ ሰራ ሄዶ ነበር። በሩን ከፈተና እንዲህ አለኝ መኪናውን መንዳት አይቻልም ወደ ጋራዥ መውሰድ ይኖርብናል"።

በሩን ዘጋሁና መሳቅ ጀመርኩ። ሆነ ብዬ ያደረግሁት ነገር አይደለም። ድንገት የሆነ ነገር ነው። ከመንፈሴ የመነጨ ነገር ነው እንደዚህ ልስቅ የቻልኩት ጠዋት እግዚአብሄር እንዲወደኝ ስላደረግሁ እንደሆነ አመለከተኝ። እግዚአብሄር እንዲወድህ ማድረግ በአንተ ውስጥ የእምነት በር እንዲከፈት ያደርጋል። ዝም ብዬ መሳቅ ጀመርኩ ይህ ነው እምነት።

አብርሃም የእምነትን ሳቅ ሳቀ። እግዚአብሄር ወደ እርሱ መጥቶ ወንድ ልጅ እንደሚወልድ ሲነግረው አብርሃም ደንግጦ ሳቀ፤ እንዲህም አለ "ክብር ይሁን! አምናለሁ!" ሣራ ግን የጥርጣሬንና የእምነተ ቢስነት ሳቅ ሳቀች እግዚአብሄርም ከስህተቷ መለሳት አብርሃምን ግን አልወቀሰውም። አብርሃምን መጥተህ ሳቅ አላለውም ምክንያቱም የእምነት ሳቅ ነበረ።

ዲያብሎስ ሲቃወምህና በአንተም ላይ ሊያደርግ ያሰበው ነገር በሙሉ የሞኝ ስራና አሰቂኝ ሲሆንብህ አምላክህን በሚገባ ስለምታውቅ የሚያስፈራህ ነገር አይኖርም በእምነት ሳቅ እግዚአብሄር እንደሚወድህ ታውቃለህ እርሱም ጉድለትህን ሁሉ ይሸፍናል።

በተበላሸው መኪናችን ጉዳይ ስስቅ እግዚአብሄር ዝግ ባለ ድምጽ ለልቤ አንድ ነገር ተናገረኝ፤ የተናገረኝ ነገር እጅግ ብርቱ ነበር። ሶስት ጊዜ እንዲህ አለኝ "ጆይስ በፊቴ የምትኖሪው እንዲህ ከሆነ ከቶ አላሳዝንሽም።"

በእግዚአብሄር ላይ የምትደገፍና እግዚአብሄርም እንዲወድህ የምታደርግ እንዲሁም አንተም የምትወደው ከሆነ የእምነት ጉዞህ ይሰምርልሃል። ከአንተ የሚጠበቀው እግዚአብሄር እንዲወድህ ማድረግና አንተም እርሱን መውደድ ብቻ ነው፤ እርሱ ሁሉንም ነገር ያሳልፍሃል። የእግዚአብሄር ፍቅር በውስጥህ ስለሚሰራ ፍርሃትን ሁሉ አውጥቶ ይጥላል።

## እግዚአብሄር ይወድሃል!

## 6. ፍቅር ለሌለው ያስባል

" እግዚአብሄርንም የሚወድ ወንድሙን ደግሞ እንዲወድ ይህች ትእዛዝ አለችን "

1 ዮሐንስ 4÷21

አንተ የእግዚአብሄር ልዩ ልጁ ነህ ። በዘዳግም 7÷6 ላይ ይህንን ሃሳብ እናገኛለን። እግዚአብሄር እንደሚወደው ሰው የምትኖር ከሆነ እግዚአብሄር በአንተ ውስጥ ዓለምን መለወጥ ይጀምራል ። ወደ ገበያ ስትሄድ ፊትህ በደስታ ያበራል የምትገዛውን ዕቃ እያነሳህ እንዲህ ትላለህ "የምነካው ነገር ሁሉ የተባረከ ነው። ሃሌ ሉያ! ዛሬ እኔን በዚህ መደብር ውስጥ ስላገኙኝ የተባረኩ ናቸው። ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን!" በመደብሩ ውስጥ እያፏጨህ እየዘመርህና በሄድክበት ስፍራ ሁሉ ራስህን የተለየህ ሰው አድርገህ እየተመለከትህ ሂድ።

የተለየን ሰዎች መሆናችንን ማወቅና እግዚአብሄርም እንደሚወዳቸው ሰዎች መኖር ስንጀምር ዓለምን ለክርስቶስ መማርክ እንችላለን። ፍቅር እንደ ሰደድ እሳት ይስፋፋል። በሰዎች ላይ እያጉረመረምህ ክርስቲያን ነኝ ብትል ለማንም አይጠቅምም። "ክርስትያን ነኝ ክርስትያን ነኝ!" ትላለህ። ነገር ግን መኪና ከፊት ለፊትህ ጥልቅ ሲል "አንተ ደደብ ከመንገዴ ውጣ። ወደ ቤተ ክርስቲያን እንደምንሄድ አታውቅም? አንተ ወፈፌ ልታስረፍድብኝ ነው" ትላለህ።

አንዳንድ ጊዜ እንዲህ የመሳሰሉ ነገሮችን እናደርጋለን። ድል ለመንሳት ዝግጁ ነህ? በመንፈስ ተራመድና ድሉን ጨብጥ እንዲህም በል "ዲያብሎስ ለብዙ ጊዜ በፍርሃት እንድኖር አድርገሃል። እኔ ልዩ ሰው ነኝ በኢየሱስ ስም ድል እነሳለሁ ምክንቱም እግዚአብሄር ይወደኛል ዲያብሎስ ከዚህ በኋላ ምንም ማድረግ አትችልም!"

በውስጥህ ያለው የእግዚአብሄር ፍቅር ከፍርሃት ነጻ ያወጣሃል ሌሎችንም በፍቅር ለማገልገል አትፈራም። እግዚአብሄር በአንተ ውስጥ ታላቅ ነገር እንደሚሰራ ሲናገር እንድታምነው ይፈልጋል ምክንያቱም ኢየሱስ ወደ አብ ሄዶአል። እግዚአብሄር አንተን ለስራው እንደሚፈልግህ ታምናለህ? እግዚአብሄር ያመንከውን ነገር ይሰጥሃል። በእምነት ለመራመድ አትፍራ።

ከፍርሃት የተነሳ ምንም ነገር መስራት ከማትችልበት የእምነት አፋፍ ላይ ስንት ጊዜ ደርሼ እንደነበር ልነግርህ አልችልም፤ እግዚአብሄር ግን እንዲህ አለኝ፤ "ተነሺ ጆይስ ተነሺ። በአንቺ ውስጥ ታላቅ ነገር እሰራለሁ"። እኔም ወዲያውኑ ዘልዬ ተነሳሁ፤ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እግዚአብሄር ጥሎኝ አያውቅም።

የእምነት እርምጃ ከጀመርኩ በኋላ ውድቀትን ለምን እንደማልፈራ ታውቃለህ? እግዚአብሄር እንደሚወደኝ አውቃለሁ። እርሱ ይወደኛል እኔም እንደምወደው ያውቃል ከእርሱም ጸጋ የተነሳ ሕይወቴን ለእርሱ ሰጥቻለሁ። ይህን አድርገህ ከሆነና አንተም እግዚአብሄርን የምትወድና እርሱም የሚወድህ ከሆነ በዚህ ዓለም ውስጥ ድል ለመንሳት የሚያስቸግርህ ነገር አይኖርም።

> "ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል? መከራ፤ ወይስ ጭንቀት
> ወይስ ስደት ወይስ ራብ ወይስ ራቁትነት ወይስ ፍርሃት
> ወይስ ሰይፍ ነውን ? ስለ አንተ ቀኑን ሁሉ እንገደላለን፤
> እንደሚታረዱ በጎች ተቆጠርን ተብሎ እንደ ተጻፈ ነው።"

> "በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን።
> ሞት ቢሆን ሕይወትም ቢሆን መላእክትም ቢሆኑ ግዛትም
> ቢሆን ያለውም ቢሆን የሚመጣውም ቢሆን ኀይላትም
> ቢሆኑ ከፍታም ቢሆን ዝቅታም ቢሆን ልዩ ፍጥረትም
> ቢሆን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ካለ ከእግዚአብሄር ፍቅር
> ሊለየን እንዳይችል ተረድቼአለሁ"።
>
> ሮሜ 8 ÷ 36-39

የአንተን ነጻ መውጣት እግዚአብሄር ምንኛ እንደሚወድህ ላታስተውል ትችላለህ። ደስተኛ ካልሆንክ እግዚአብሄር በዚህ ያዝናል አንዳንድ ጊዜ በመጥፎ ስሜት ውስጥ ታሳልፋለህ። የትኛውን ቀን እንደምል ሳትገምት አትቀርም? ድመቷን ታባርራለህ ልጆችህ ላይ ትጮሃለህ ጎረቤቶችህን ትሰድባለህ ያ የድሮ ባሕርይህ ይመጣብህና ፊትህ ጭፍግግ ይላል። "የምሰራውን ሥራ ማንም ሰው አያመሰግንም" በማለት ትማረራለህ።

እንዲህ ለምን እንደምትሆን ይገባኛል፤ እኔም በዚህ ውስጥ አልፌአለሁ ልጆችህ ወደ ቤት ሲመጡ “ትምህርት ቤት ሰባት ሰዓት በመቆየት ፋንታ አስራ አራት ሰዓት ለምን አልቆዩም?” ብለህ ትነጫነጫለህ፡፡

ይህ እግዚአብሄርን እንደሚያሳዝነው ታውቃለህ? መጥፎ ስሜት እንዲሰማህ እያደረግሁ አይደለም፡፡ እግዚአብሄር እንደሚወድህ ካመንህ ለዚህ ፍቅር ምላሽ መስጠት እንዳለብህ እንድትገነዘብ እየረዳሁህ ነው ይህ ፍቅር ልብህን በመሙላት በሰዎች ሁሉ ላይ መፍሰስ ይጀምራል ነጻና ደስተኛ ሰው ትሆናለህ መልካምነትም ከአንተ ይፈልቃል፡፡

እግዚአብሄር በእርግጥ እንደሚወድህ ካመንህ ፈውስ ታገኛለህ ብልጽግና ታገኛለህ የሚያስፈልግህንም ታገኛለህ፡፡ ለምን? ምክንያቱም እግዚአብሄር ይወድሃል፡፡ ስለዚህ በእርሱ ላይ መደገፍን ተማር፡፡

እግዚአብሄር ሊሰጠን የሚፈልጋቸውን ብዙ ነገሮች የማይሰጥበት ምክንያቱ በእርሱ ላይ በመደገፍ ፋንታ በራሳችን ለማግኘት አገር ምድሩን ስለምንባጥጥ ነው፡፡ እግዚአብሄር በእርሱ ላይ እንድታርፍና እርሱንም እንድትወድ ይፈልጋል፡፡ እርሱ እንዲወድህ እንድትፈቅድለትና ከእርሱም እንድትቀበል ይፈልጋል፡፡

ሰዎችን የምትወድ ከሆነ ዲያብሎስ ከውስጥህ የሚፈሰውን ፍቅር ሊያስቆም አይችልም ምክንያቱም ሰዎችን ስትወድ ሰጪ ትሆናለህና አለመስጠትም ከቶ አትችልም፡፡

የዘዳግም 7÷6 የመጨረሻው ክፍል እንዲህ ይላል “ለራሱ ሕዝብ ትሆን ዘንድ አምላክህ እግዚአብሄር መረጠህ”፡፡ እግዚአብሄር ጠርቶሃል በአሁኑ ሰዓት ትልቁ ሥራህ በቤት ውስጥ ከቤተሰብህ ጋር መሆን ሊሆን ይችላል ነገር ግን እግዚአብሄር ጠርቶሃል፡፡ እግዚአብሄር በአንተ እንዲሰራ የምትፈልግ ከሆነ እግዚአብሄር በአንተ ሊሰራ ይችላል፡፡ ነገር ግን በቅድሚያ ይህን መሰረት መመስረት አለብህ፡፡ እግዚአብሄር እንደሚወድህ እወቅ፡፡

መንፍሳዊ ኃይልህን በሙሉ በራስህና በፍላጎቶችህ መሟላት ላይ አታውል፡፡የምትፈልገውን ነገር ለእግዚአብሄር ንገረው፡፡ ከዚያም ለሌሎች የሚያስፈልጋቸውን ለመሙላት የሚያስችልህን እምነት አጎልብት፡፡ ኢየሱስ ወደ እርሱ የእምነት ትምህርት ቤት የሚመጡ ሰዎች ለሌሎች የሚያስፈልጋቸውን ለመሙላት የሚያስችላቸውን እምነት እንዲያገኙ ይፀልያል የእግዚአብሄርንም ፊት ይሻል፡፡

ከዚያም ቃሉን ይሰብክላቸዋል እጁን በላያቸው ይጭናል፤ እነርሱም ተአምር ይቀበላሉ፡፡ እግዚአብሄር የሚፈልገውን ነገር እንዲሰጠው አንዱ ጥግ ዝም ብሎ አይቀመጥም፡፡ ምን እንደምትፈልግ ለእግዚአብሄር መናገር አለብህ፡፡ ይሁንና የምትፈልገው ነገር እግዚአብሄርን የሚያከብር ሊሆን ይገባል፡፡ ማለትም የልብህ መሻት ለሌሎች ሰዎች የሚያስፈልጋቸውን ነገር መሙላት መሆን አለበት፡፡

እውነተኛ ብልጽግና በትክክል ይተርጎም ከተባለ ለሌሎች ሰዎች የሚያስፈልጋቸውን ነገር በመሙላት እግዚአብሔር የሚሰጠንን በረከት በአግባቡ መጠቀም ማለት ነው፡፡ የእግዚአብሔር ፍቅር የሌሎች ሰዎችን ችግር እንድታስቀድም አቅም ይሰጥሃል፡፡ እግዚአብሔር ሊወደዱ የማይገባቸውን ሰዎች ለምሳሌ ጨቅጫቆችንና ምስጋና ቢሶችን ለመውደድና ችግራቸውን ለመሙላት እንድትችል ወዶኛል ብለህ ታምናለህ፡፡

የሚወዱህን ሰዎች መውደድ ከባድ አይደለም፡፡ ለዚህም ምስጢር የለውም፡፡ ምክንያቱም ማንኛውም ሰው ይህን ማድረግ ስለሚችል፡፡ ነገር ግን በስራቸው ሊወደዱ የማይችሉ ሰዎችን ስትወድ በተደጋጋሚ ስትወዳቸው የእግዚአብሔር ፍቅር ይለውጣቸዋል፡፡

ይህ ዓመታት ሊወስድ ይችላል፡፡ አምስት ዓመት ሊወስድ ይችላል ሃያ አምስት ዓመት ሊወስድም ይችላል፡፡ ይሁንና እንዲህ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ ኢየሱስ አንተን የጠበቀህ ለምን ያህል ጊዜ ነው?

እግዚአብሔር ይወድሃል ደግሞም በአንተ ዙሪያ ያሉ ሰዎችንም ሁሉ ይወዳቸዋል፡፡ የዳኑትንም ሆነ ኃጢያተኞችን ይወዳቸዋል ደግሞም እርሱ የፍቅሩ መገለጫ አድርጎ በአንተ አማካይነት ሊሠራ ይፈልጋል፡፡

በእምነት ለመራመድ አትፍራ። የእግዚአብሔር ፍቅር ከፍርሃትና ከኩነኔ ነጻ አውጥቶሃል ሌሎችን መውደድ እንድትችል አቅም ሰጥቶሃል። የእግዚአብሔርን ፍቅር በዙሪያህ ላሉ ሁሉ ለማወጅ ቆርጠህ ተነሳ። ከሰዎች ጋር ወዳጅ ለመሆን ሞክር። ከሰዎች ጋር ወዳጅ ለመሆንና በክርስቶስ አካል ውስጥ ላሉት ሁሉ በረከት ለመሆን የዘወትር ሥራህ ይሁን።

ሰዎች በቤትህ መጥተው እራት እንዲበሉ ወይም አንዲጐበኙህ ጋብዛቸው። በደስታ የተሞላ ሰላምታ ስጣቸው። እግዚአብሔር በአንተ ውስጥ ሊሠራ የሚፈልገው ነገር አለ። በዚህ ምድር ባሉ በሌሎች ሰዎች ሊሠራ የማይፈልገውን ነገር በአንተ አማካይነት መሥራት ይፈልጋል።

አንተ ብቻ ልታገለግላቸው የምትችል ሰዎች አሉ። እንደዚህ ያሉ ሰዎችን ከአንተ በስተቀር ሌላ ማንም ሊደርሳቸው አይችልም። እግዚአብሔር በፍቅር እንዴት እንደምታገለግላቸው እንዲመራህ ጠይቀው እርሱም ያስተምርሃል።

## እግዚአብሔር ይወድሃል!

# 7.የእግዚአብሔር ፍቅር ይለውጥሃል

> "ፍቅር እንደዚህ ነው እግዚአብሔር እራሱ እንደ ወደደን
> ስለ ኀጢያታችንም ማስተሰሪያ ይሆን ዘንድ ልጁን
> እንደ ላከ እንጂ እኛ እግዚአብሔርን እንደ ወደድነው አይደለም።"
> 1ዮሐንስ 4፡10

እግዚአብሔር ይወደናል ሆኖም ብዙዎቻችን እርሱ እኛን የወደደበትን ፍቅር ሙሉ በሙሉ ተገንዝበነዋል ብዬ ለማለት አልደፍርም። ስለዚህ ጉዳይ ጥናት ሳደርግና እግዚአብሔርም እንደተናገረኝ እግዚአብሔር ምን ያህል እንደወደደን በመንፈሳችን ብናስተውል አሁን እየኖርን ካለነው ሕይወት የተሻለ እንኖር ነበር።

የእግዚአብሔርን ፍቅር ዘወትር አሰላስል። ምክንያቱም የሚለውጥህ ይህ ነው። ስለ ራስህ የማትወደው ነገር ቢኖርህ እግዚአብሔር እንደሚወድህ ካወቅህ እርሱ ይለውጥሃል።

አንድ ሰው እንደሚወድህ ስታውቅ የሚሰማህ ስሜት ምንድን ነው? በጣም ደስ ይልሃል አይደል? መጥፎ ስሜት የሰማሃል? እግዚአብሔርንይህን መጽሐፍ የሚያነቡ አንዳንድ ሰዎች ራሳቸውን እንደሚጠሉ ነግሮኛል። የምታደርገውን ነገር ትጠላለህ? አዲስ ፍጥረት መሆንህን ለመቀበል አልቻልክም ከአሮጌው ባሕርይ ጋር እየተፋለምህ ነው። ሁልጊዜ ስለ ራስህ መጥፎ ስሜት እየተሰማህ የምትኖር ከሆነ፣ እንዲሁም ራስህን የማትውድ ይልቁንም የምትጠላና የተለየህ ስው እንደሆንህ የማትቀበል ከሆነ፣ ልዩ በሆነ መንገዱ ልታገለግል አትችልም። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፤ “በልቡ እንዳሰበ እንዲሁ ነውና”። ይህ የሚያሳየው አሁንም እግዚአብሔር እንደሚወድህ ገና ያልተረዳህ መሆንህን ነው። እግዚአብሔር እንደሚውድህ ማስተዋል እጅግ ታላቅ ነገር ነው።

እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ኅብረትን በየዕለቱ እንድታደርግ ይፈልጋል:: የአንተ ለውጥም በዚህ ውስጥ ነው ያለው። እግኢአብሔርን በሕይወትህ የማታስቀድም ከሆነ በአንተ ላይ ያለውን አላማ ትከለክላለህ ከእግኢአብሔር ጋር ሕብረት የምታደርግበት የግል ጊዜ ይኑርህ እርሱን ውደደው እርሱም እንዲወድህ ፍቀድለት በመንፈዊ ሕይወትህ እንድታድግና እንድትበረታ የሚያስችልህ ይህ ነው።

ብዙ ሰዎች ሰነፎች በመሆናቸው ይህን ባያደርጉ ይመርጣሉ። አንድ ሌላ ሰው በእነርሱ ምትክ ቢያደርግላቸው ይመረጣሉ። ሰበብ አታብዛ ይህ ጸሑፍ የሚያነብና ከእግኢአብሔር ጋር ኅብረት የሌለው ሰው ከዚህ ጸሑፍ የተነሣ ቢወቀስ ዲያብሎስ “እነዚህ ሁሉ ሥራዎች የሚጠብቁት እኮ አንተንነው” በማለት ሊከሰው ይችላል ።

ነገሩ ወዴት ለየመራ እንደሚችል ግልጽ ነው፡፡ ዲያብሎስ በአንዱ ሰበብ ላይ ሌላውን ሰበብ ያቀርብልሃል፡፡ እግኢአብሔርን ለማወቅ ቆርጠህ ተነሳወደ እርሱም ጨህ የእግዚአብሔር ቃልና ከእርሱም ጋር ኅብረት ማድረግ ይለውጥሃል፡፡ እግኢአብሔር አስችሎት ይሰጥሃል፡፡ ጳውሎስ በፊልጵስዩስ 4÷13 ላይ እንዲህ ይላል "ሃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ"፡፡ በሌላ አነጋገር በዚህ ዓለም በክርስቶስ ኢየሱስ ኃይል የማታደርገው አንዳች ነገር የለም፡፡

በአንተ ውስጥ ያለውን ችግር እግዚአብሔር ካመለከተህ በቶሎ እርምጃ ውሰድና ችግሩን በድል ተጋፈጥ፡፡ የእግኢአብሔርን ፍቅር በእምነት የምትቀበልና የዲያብሎስን ከንቱ ንግግር እና እንደማትረባ የሚናገረውን ቃል የምትቃወም ከሆነ በድል አድራጊነት ትራመዳለህ፡፡

አሁን በጣም መጥፎ ሁኔታ ውስጥ ትሆን ይሆናል ነገር ግን በውስጥህ አዲስ ፍጥረት እንደሆንህ የምታምን ከሆነ የተለየ ሕይወት ትኖራለህ፡፡ ተነሥተህ "እግዚአብሔር ይመስገን የተለየሁ ሰው ነኝ "እስከምትል ድረስ አንድም ነገር ማድረግ አትችልም፡፡ እግዚአብሔር መርጦኛል፡፡ በበጉ ደም አንጽቶኛል፡፡ እንደ ተመረጠና እንደ ነጻ ሰው መኖር አለበኝ፡፡ ዲያብሎስ ብዙ ስህተቶችን ብፈጽም ግድ የለኝም:: እግዚአብሔር ከውድቀቴ ሊያነሳኝና ሊያስቀጥለኝ ይችላል፡፡እርሱ ያበላሸሁትን ነገር ሁሉ ያስተካክላል!

እግዚአብሔር እንደሚወድህ ካወቅህ ምን አይነት ችግር ሊያሸንፍህ ይችላል? ሊያሸንፍህ የሚችል አንድም ችግር የለም፡፡ በሁሉ ነገር ድል ትነሳለህ፡፡ አሸናፊ መሆን ትፈልጋለህ? እንግዲህ ይህን ጥያቄ መልስ ልታሸንፈው የምትፈልገው ነገር አለ? ልታድግ የምትችለው በዚህ መንገድ ብቻ ነው፡፡ ምንም ዐይነት ችግርና የምታሸንፈውም ነገር ከሌለህ እምነትህ ሊያድግ የሚችለው እንዴት ነው?

የሕይወት ገጠመኞችህን የመነሻ የእድገት መንገድ እንዲሆኑ አድርገህ ቁጠራቸው፡፡ እግዚአብሔር ስለሚወድህ በአንተ ሊሠራ የሚፈልገውን ነገር ተረዳ፡፡

በእግዚአብሔር ላይ የምትደገፍ እርሱም እንዲወድህ የምትፈቅድና አንተም የምትወደው ከሆነ በራስህ የምታደርገውን ሩጫ አቁመህ ወደ እረፍቱ ትገባለህ፡፡

እግዚአብሔርን የምትወድና እንደሚወድህ የምታውቅ ከሆነ በመንፈስ እንደ ሰከረ ሰው ትሆናለህ፡፡ በዚህ ጊዜ በሕይወት በሚገጥሙህ ችግሮች ድል አትነሳም ምክንያቱም በፍቅሩ መኖር ጀምረሃልና፡፡

በመንፈስ ቅዱስ ስጠመቅ ለመጀመሪያዎቹ ሶስት ሳምንታት በእግዚአብሔር ፍቅር እንደ ሰከረ ሰው ሆኜ ነበር፡፡ ሰዎች እንዲህ ይሉኝ ነበር "ጆይስ ምን አዲስ ነገር አገኘሽ? በጣም ልዩ ሰው ሆነሻል፡፡ ለማመን ያስቸግረኛል፡፡ በሕይወትሽ የተፈጠረው ምንድነው?" ከሶስት ሳምንት በኋላ እነዚህ ሰዎች ወደ እኔ መጥተው እንዲህ አሉኝ፣ "በሕይወትሽ የተፈጠረው ነገር ምንድን ነው ?"

መለወጤን ለእነርሱ ማስረዳት አላስፈለገኝም፡፡ ሊያዩት ይችሉ ነበር:: በእግዚአብሔር ፍቅር የምትኖር ከሆነ ሁልጊዜ ደስተኛ ትሆናለህ፡፡ ውብ ሰው ትሆናለህ፡፡ ኃይልና ብርታት ይኖርሃል፡፡ ሰዎችን ለማገልገል የምትቀና ትሆናለህ ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ ይህን ለማድረግ ኃይል ይሰጥሃል የሚያስፈልግህንም ነገር አብዝቶ ይቸርሃል፡፡

ለራስህ እንዲህ በል "እግዚአብሔር ይወደኛል፡፡ ሃሌሉያ እግዚአብሔር ይወደኛል፡፡ እኔ የተለየሁ ልጁ ነኝ፡፡ እግዚአብሔር ይወደኛል!" አሁን ፀንተህ ቁም፣ በእምነት ተራመድ፣ እመን፡፡

እግዚአብሔር በእርግጥ ይወድሃል!
አዲስ ሕይወት ተለማመድ

ኢየሱስን ጌታና አዳኝ አድርገህ ወደ ልብህ ካልጋበዝከው የሚከተለውን እንድታደርግ እጋብዝሀለሁ፡፡ የሚከተለውን ፀሎት አብረህ እንድትፀልይ እጋብዝሃለሁ፡፡ ከልብህ የምትፀልይ ከሆነ በክርስቶስ አዲስ ሕይወት ታገኛለህ፡፡

እግዚአብሔር አባት ሆይ፣ የዓለሙ አዳኝ
በሆነው በልጅህ በኢየሱስ ክርስቶስ አምናለሁ
በመስቀል ላይ ስለ እኔ እንደሞተ አምናለሁ፣
ኃጢአቴን ሁሉ እርሱ ተሸከመ። ወደ ሲኦል ወረደ፣
በሞትና በሲኦል ላይ ድል ነሣ። ኢየሱስ ከሙታን
እንደተነሣና በአንተም ቀኝ እንደተቀመጠ አምናለሁ።
ኢየሱስ ሆይ እፈልግሃለሁ። ኃጢአቴን ይቅር በል፣
አድነኝ በእኔ ውስጥ ለመኖር ወደ ሕይወቴ ና።
ዳግመኛ መወለድ እፈልጋለሁ።

አሁን ኢየሱስ በውስጥህ እንደሚኖር እመን። ይቅር ተብለሃል ፀድቀሃል ወደ መንግሥተ ሰማይም እንድትገባ ተደርገሃል።

የእግዚአብሔርን ቃል የምትማርበት አጥቢያ ቤተክርስቲያን በአካባቢህ ፈልገህ ወደዚያ ሂድ፣ በክርስቶስም እደግ።  ያለ እግዚአብሔር ቃል መረዳትና እውቀት የሕይወት ለውጥ እድገት አይገኝም። ዮሐንስ 8÷31-32 እንዲህ ይላል፣ "እናንተ በቃሌ ብትኖሩ በእውነት ደቀ መዛሙርቴ ናችሁ። እውነትንም ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል"።

የእግዚአብሔርን ቃል አጥብቀህ እንድትይዘው እመክርሃለሁ በልብህ ውስጥ ትከለው። በ2ቆሮንቶስ 3÷18 መሠረት ወደ ቃሉ በተመለከትህ ቁጥር የኢየሱስ ክርስቶስን መልክ እየመሰልህ ትሄዳለህ።

ኢየሱስንም እንደ ግል አዳኝ አድርገህ ወደ ልብህ ካስገባህ በኋላ ሁኔታህን በደብዳቤ ጻፍልኝ።  በክርስቶስ አዲስ ሕይወት እንዴት መኖር እንደምትችል የሚያስተምርህን መጽሐፍ በነጻ እንድልክልህ ጠይቅ። ጻፍልኝ

በጌታ ፍቅር
ጆይስ

## ስለ ደራሲዋ

ጆይስ ማየር የእግዚአብሔርን ቃል ከ1976 ዓ.ም. ጀምሮ ሲያስተምሩ ቆይተው በሙሉ ጊዜነት ከ1980 ዓ.ም. ጀምሮ ለአገልግሎት ተለዩ:: ብዙ ተፈላጊነት ያላቸውን ከስልሳ በላይ መጻሕፍትን አሳትመዋል:: ከእነዚህም መካከል "ሰላምን መፈለግ የእግዚአብሔርን ድምጽ መስማት "እግዚአብሄርን ማወቅ" እና "ኀሊና መፋለሚያ ሜዳ" የሰኙት ይገኙበታል።" ከዚህም በተጨማሪ በሺህ የሚቆጠሩ የቴፕ እና የቪዲዮ ካሴቶችን አሰራጭተዋል። የጆይስ "enjoying everday life" የተሰኘው የሬዱዮና የቴሌቪዥን ፕሮግራም በመላው ዓለም ይሰራጫል። በብዙ ቦታ እየተዘዋወሩ በመንፈሳዊ ፕሮግራሞች ላይ ያስተምራሉ። ጆይስና ባለቤታቸው ቤቭ የአራት ልጆች ወላጅ ሲሆኑ የሚኖሩትም በሚዙሪ ሴንት ሉዊስ በሚባል ስፍራ ነው።

## የእግዚአብሔርን ስጦታ መቀበል ወሰን የለሽ ፍቅር

እግዚአብሔር ኃይሉንና ፍቅሩን ዛሬውኑ ሊሰጥህ ይፈልጋል። አንተ ከብዙ ሕዝብ መካከል አንዱ ነህ እግዚአብሔር በዚህ ምድር የምትኖረው አንተ ብቻ እንደሆንህ አድርጎ ይወድሃል ችግሩ እንደ ሌሎቹ ብዙ ሰዎች አንተም ነገሩን አታስተውለው ይሆናል። ወይም ደግሞ ነገሩን በአእምሮህ ብትረዳው በልብህ አይሰማህ ይሆናል አሁን ልታስተውለው ትችላለህ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የምታነባቸው ነገሮች የሚከተሉትን እውነቶች ያስገነዝቡሃል።

- የእግዚአብሔርን ፍቅር እንዴት መረዳት እንደምትችል
- የእግዚአብሔርን ድንቅ ፍቅር በሕይወትህ እንዴት እንደምታይ
- በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ እግዚአብሔርን እንዴት እንደምታገኝ
- የእግዚአብሔር ፍቅር እንዴት ለዘላለም እንደሚለውጥህ

ጆይስ ማየር የእግዚአብሔርን ፍቅር ማስተዋል እንድትችል ሕይወታቸውን የለወጠውን መገለጥና እውነት ያካፍሉሀል የእግዚአብሔርን ቃልና ሌሎች የጥበብ ቃሎችን ወደ አንተ ያደርሱልሃል ብርሃኑ በሕይወትህ ይብራ!

## እግዚአብሄር ምን ያህል እንደሚወዳችሁ ታውቃላችሁ?

"እግዚአብሄር ይወዳችኃል" የሚለውን አባባል ምናልባት ብዙ ሰምታችሁ ይሆናል፡ ፡፡ አዎን ሰዎች እንዲያውም እንዲህ ብለው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ይጠቅሳሉ "እግዚአብሄር ዓለምን ሁሉ ወዷል" ደግሞም "እግዚአብሄር ፍቅር ነው"፡፡ ጥያቄው እግዚአብሄር ያለገደብ እንደወደደን ይረዳሉ? ሁልጊዜ? ምንም ቢሆን ምንም? የተፈጠርንበትን ማንነት እንድንሆንና እንዳቀደው ሁሉን ማድረግ በነጻነት እንድንችል ይህ እውነት በየለቱ በሂዎታችሁ ለውጥ ያመጣል?

በዚህ አስደናቂ ትምህርት ፡-

- መጽሐፍ ቅዱስ በእርግጥ ስለ እግዚአብሄር ፍቅር ምን እንደሚል ትመረምራላችሁ፤
- የእግዚአብሄርን ፍቅር እንዴት መቀበልና ለሌላው መስጠት እንደምትችሉ ትማራላችሁ፤
- የህይወት ለውጥ እንዴት እንደሚያመጣም ልምድ ትቀስማላችሁ፤
- በየለቱ በእግዚአብሄር ፍቅር መኖርን ትረዳላችሁ፡፡

ይህ መልዕክት በክርስቶስ ለሚያምኑና ከእርሱ ጋር የጠለቀ የግል ህብረት ለማድረግ ለሚፈልጉ፤ እግዚአብሄር የሰጣቸውን ብቃትና አላማ ለመፈጸም ለሚሹ ሁሉ እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡ በእግዚአብሄር ባላችሁ እምነት አዲስ ብትሆኑም ወይንም በርካታ አመታት ብታስቆጥሩም፤ ከምታስቡት በላይ የላቀ ፍቅሩን ስለምትቀምሱ ወደ እርሱ ይበልጥ እንድትጠጉ አዲስ ነገር ትማራላችሁ!